*ልዩ ዘገባ*

## የኢሕአፓ በዓል በፍራንክፈርት --

## የትውልድ ትውስታ አድናቆትን አተረፈ

ባለፈው ቅዳሜና እሁድ ኦገስት 22 ና 23 ቀን 2009 ዓ.ም. በፍራንክፈርት ከተማ የኢሕአፓ 37ኛው የምስረታ ዓመት በዓል በትግል የተሰዉትን ውድ አባላቱንና ደጋፊዎችን በመዘከር የተከበረ ሲሆን ከዚሁ ጋር ተያይዞ በጀርመን የኢሕአፓ ደጋፊ ኮሚቴ መደበኛ አመታዊ ስብሰባው ተካሂዶ "የትውልድ ትውስታ" የተሰኘውና ከፍተኛ አድናቆትን እያተረፈ ያለው ፊልምም ታይቷል። የዘንድሮዉን በዓል ልዩ ካደረጉት ሁኔታዎች አንዱ የወጣቶች ድርጅት ማለትም ኢ.ሕ.አ.ፓ.ወክንድ ተወካይ በበዓሉ ተገኝቶ ቀስቃሽ መልዕክት ማስተላለፉና ለቀረቡት ጥያቄዎችም ምላሽ መስጠቱ ነው።

በደመቀ ሁኔታ በተሰብሳቢዎቹ "የትግሉ ነው ሕይወቴ" መዝሙር የታጀበውና ለበዓሉ ከኢ.ሕ.አ.ፓ ከፍተኛ አመራር ኮሚቴ የተላከው መልዕክት በኮሚቴው አባል በጓድ ዶክተር ዘነበ ተሾመ ተነቧል። ሲነበብ በጓድ አሊ ሰዒድና የትግል ጓዶቹ ታሪክ ዙሪያ የሀገራችንን የትግልና የሽብር ዘመን የሚያቀርበውና በቅርቡም በኢጣሊያ ሁለት ሽልማቶችን ያገኘው የትውልድ ትውስታዎች ፊልም ታይቶ ከፍተኛ አድናቆትን ሲያተርፍ በግፍ ሕይወታቸው እንዲያልፍ የተደረጉትን የዛን ትውልድ አባላት ስቃይ በፊልም ተቀርጾ ለታሪክ መቀመጡ መልካም እርአያ እንደሆነ ሲገለጽ በሌላ በኩል ደግሞ ውስጣዊ ሀዘንንም በተመልካቹ ልብ ውስጥ መቅረጹ ተስተውሏል። ፊልሙን ለተሰብሳቢው ያቀረበውና ማብራሪያ የሰጠው ጓድ አሊ ሰዒድም በበአሉ አዘጋጆች የተዘጋጀለትን የመታሰቢያ ስጦታ ከጓድ ገነት ግርማ እጅ ተቀብሏል። ጓዲት ገነት ግርማም በስጦታው ወቅት አቶ አሊንና ቤተሰቦቹን አስመልክቶ በተለይም የአቶ አሊ ሴት ልጅ ወይዘሪት ምሳሌ የታሰሩ አበራሽ በርታንና መሰሎችን አስመልክቶ ያደረገችውንና እያደረገች ያለችውን እንቅስቃሴ የምስክር ቃላቸውን ለተሰብሳቢው አሰምተዋል።

ወጣቱ የኢ.ሕ.አ.ፓ.ወክንድ ተወካይ ደግሞ ተመሳሳይ የመታሰቢያ ስጦታ ከኢ.ሕ.አ.ፓ አመራር ኮሚቴ አባል ከጓድ ኢያሱ አለማየሁ ተቀብሏል።

በአጠቃላይ የበዓሉ መንፈስና የደጋፊ ኮሚቴውም ስብሰባ ብሩህ ተስፋን ያንጸባረቀ መሆኑ ታይቷል። እሁድ ተሰዓት በኋላም የ"ትውልድ ትውስታዎች" ፊልም በድጋሚ ለተመልካቾች ቀርቧል። ይህ ፊልም ጓድ አሊ በሚገኝበት በሰሞኑ በስቶክሆልም፤ ስዊድንና በኦስሎ ኖርዌይም ለሕዝብ እንደሚታይ ተውቋል።

በበዓሉ ወቅትም ለፍኖተ ዴሞክራሲ ራዲዮ መርጃ የተሰናዳው ቶምቦላ ወጥቶም የሚከተሉት አሸናፊ ሆነዋል።

- 1ኛ የወጣውና ላፕ ቶፕ ኮምፕዩተር ያገኘው ቁጥር 003234 ከኦሻኒያ
- 2ኛ የወጣውና እችዲቲ ቴሌቪዥን የሚያገኘው ቁጥር 004488 ከሰሜን አሜሪካ
- 3ኛ የወጣውና አይፖድ የሚያገኘው ቁጥር 004485 ከሰሜን አሜሪካ ሲሆን
- የማስተዛዘኛ ሽልማት ያገኘው 003108 አሁንም ከኦሻኒያ ናቸው። አሸናፊዎቹም በቶምቦላው ያገኙትን በቅርብ ጊዜ ውስጥ እንደሚደርሳቸው ተገልጧል።

በዛ ትውልድ አባላት የተደረገው ትግል ለኢትዮጵያ ህዝብ ቀናውን ለማምጣት ሲል የተሰዋ መሆኑ አጽንዖት በተሞላበት መልክ በጓድ አሊ ሲነገር ቀጣዩንና ሁለተኛውን ፊልምም ለማሰራት በዝግጅት ላይ መሆኑን በመግለጽ ለዚህም የሁሉንም ትብብር እንደሚያስፈልግ ከፍተኛ የአደራ ጥሪ ለተሰብሳቢውና ለሁሉም ኢትዮጵያዊ ጥሪ ቀርቧል። በመጨረሻም የመዝናኛ ሰአቶች ተደርገው የእለቱ ትዕይንት ተከናውኖ በሚቀጥለው ዝግጅት ለመገናኘት በመስማማት ተፈጽሟል።

23.08.2009